# ጸሎተ ሃይማኖት

ሁሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታይና የማይታየውንም በፈጠረ፥ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር በነበረ፥ የአብ አንድ ልጁ በሚሆን፥ በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን። ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ፥ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ፥ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል፥ ሁሉ በርሱ የሆነ ያለ እርሱ ግን ምንም ምን የሆነ የለም። በሰማይም ያለ፥ በምድርም ያለ፥ ስለኛ ስለሰዎች ስለመዳናችን ከሰማይ ወረደ፥ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፥ ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ፥ ሰው ሁኖ በጰንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለኛ ተሰቀለ፥ ታመመ፥ ሞተ፥ ተቀበረም። በሶስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፥ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፥ ዳግመኛም ሕያዋንንና ሙታንን ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል፥ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም፥ ጌታ ማኅየዊ በሚሆን ከአብ በሠረጸ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፥ እንሰግድለት እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት የተናገረ፥ ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት ባንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም እናምናለን፥ ኃጢአትን ለማስተስረይ ባንዲት ጥምቀት እናምናለን፥ የሙታንንም መነሳት ተስፋ እናደርጋለን፥ የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ አሜን።